# እነ ኣለም ዘጠኝ

እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ትውልድ ጤፉ፣
የሃገሬን ባንዲራ ሲቆርጡ ሲሰፉ፣
ሲቀዱ ሲጥፉ፣
መልኳን ኣዥጎርጉረው፣
ክብሯን ኣጭበርብረው፣
ዘጠኝ ቦታ ቆርጠው ሃገሬን ኣጠፉ፣

በጎጥ ልክፍታቸው በጎሳ ሸንሸነው  ልዩነት ለፈፉ:
የዛር ፈረስ ጭነው ነፍጥ እየሰበቁ፣ ልጆቿን ቀጠፉ።

እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ሃገር ለምኔ፣
የህጻናቱን እንባ የባልቴቷን ወይኔ፣
የኣዛውንቱን ምሬት እሪታና መጥኔ፣
የደሃውን ስደት ረሃብና ጠኔ፣

በጥብጠው ደቁሰው በእንባ እያማሰሉ፣
ህብረ ቀለም ፈጥረው ባንዲራ ሲስሉ፣
ጎሳ ሲቀልሱ ብሄር ሲቀይሱ፣
ልዩነት ሲምሱ ኣንድነት ሲያፈርሱ፣
ዘመኑ ባተና እስራው ምእት ኣልፎ ዛሬ ላይ ደረሱ።
ሁሌ እንደጨፈሩ ሁሌ እንደደነሱ ሁሌ እንደነገሱ።

እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ምርጫ ጠሩ፣
ዴሞክራሲ እያሉ ወግን ሲያሳምሩ፣
ምርጫና ጥይትን ባንድ ላይ  ሲያዘምሩ፣
ኮሮጆ ገልብጠው እየመዘበሩ፣
ከስልጣን ተጣብቀው እዛው ደርቀው ቀሩ።
እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ኣባ ሽብሩ፣
ሰው በተስፋ ላይኖር በገዛ ሃገሩ፣
ከቀዬው ሲነቅሉት ከሃገር ሲያባርሩ፣
በህግ ሲጫወቱ ፍትህን  ሲሽሩ፣
የልማትን መዝሙር ሰርክ እየዘመሩ፣
ህዝቡን ኣደህይተው እነሱ ሲከብሩ፣
ኖረው ሳይማሩ ወይ ሳይመከሩ፣
እንደዚሁ ቀሩ።

እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ልማት ብርቁ፣
በሌለ ሰማይ ላይ ከዋክብት ሲያደምቁ፣
በባዶ ህዋ ላይ ጸሃይን ሲያሰርቁ፣
ተስፋን ሲሰንቁ፣
ከእውነት ከሃቅ ጋር ሳይተዋወቁ፣
ወሬ ብቻ ሆነው መስማት ተስኗቸው ኣመታት ዘለቁ።

እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ኣባ ምትኩ፣
ስልጣንን ርስት ኣርገው እየተተካኩ፣
በእኩይ ኣላማቸው ትውልድን ሲያውኩ፣

ዱላና ጠመንጃ እየተቀባበሉ፣
ስልጣን ላይ ሊከርሙ ዙፋን ላይ ሊበቅሉ፣
በዴሞክራሲ ስም ተገዝተው ማሉ።

እነ ኣለም ዘጠኝ እነ ረሃብ  ስንቁ፣
ሃገር እንዳወኩ ህዝብን እንደናቁ፣
በብዙሃን እንባ እንደተጠመቁ፣
ዘመን ተሻገሩ ኣመታት ዘለቁ።

እነሱና ህዝቡ ሳይገጥም ኮከባቸው፣
ላይሰሙ ደንቁረው በገዛ ድምጻቸው፣
ረሃብ ሲጠራ የልማት ቋንቋቸው፣
ጠኔን ሲያከለፈልፍ የእድገት ዲስኩራቸው፣
ይኸው ዛሬም ኣሉ ሽፍጥ ተጠናውቷቸው
ዕብሪት ነግሶባቸው።
ግና እነዚህ ሰዎች እስቲ እንጠይቃቸው፣
ምን ኣይነት ቆሌ ነው የሰፈረባቸው፣

ከእውነት ኣጣልቶ ከህዝብ ለያይቶ፣
እንዲህ የሚያስጎራቸው።
በጥላቻ ሞልቶ በዘር ኣጠልሽቶ፣
ንቀት ማዋረድን የሚያቀረሻቸው።

ከያ.በ / መስከረም 2005    kiyakido@yahoo.com